K

# 2007-2008 የመዋእለ ህጻናት ማመልከቻ መመሪያዎች

ለ2007 2008 የትምህርት ዘመን ለማመልከት የመዋእለ ህጻናት ማመልከቻን ይጠቀሙ። ተጨማሪ መረጃዎች ለማግኘት እባክዎትን የ2007 2008 ምዝገባ የወላጆች መመሪያ መጽሄትን ይመልከቱ ወይም የመመዝገቢያ ማእከልን ይጎብኙ።

**ክፍል 1 –** ልጅዎ የሚኖርበት አድራሻ ይጻፉ(የቤትዎ ኣድራሻ)። ልጅዎ የሚኖርበት ከአንድ በላይ የተለያዩ አድራሻ ካለው/ካላት በተለይ በተቀዳሚነት የሚኖሩበትን አድራሻ ይጻፉን።

**ክፍል 2 –** ይህ ማመልከቻ ለመዋእለ ህጻናት ብቻ ተጠቀሙ

**ክፍል 3 (አማራጭ) –** ከየቤትዎ አድራሻ ምትክ የቻይልድ ኬር አድራሻ ለመስጠት የምትፈልጉ ከሆነ ብቻ ይህንን ክፍል ሞምላት ትችላላችሁ። የቻይልድ ኬር አድራሻ እንደ አገልግሎት አድርሻ ነው የሚታሰበው እና ይህ አድራሻ መስጠት የምትችሉት ልጅዎ የትራንስፖርት እና ሌሎች አገልግሎት ለማግኘት ብቁ ከሆነ ብቻ ነው። ልጅዎ ለቦታ ምደባ ቅድሚያዎች ሊያገኝ የሚችለው በምትሰጡት የቻይልድ ኬር አድራሻ ሳይሆን ውሳኔ የሚሰጠው በምትኖሩበት የቤታችሁ አድራሻ መሰረት ብቻ ነው።

**ክፍል 4 (አማራጭ) –** ወንድም ወይም እህት በሚመሩበት ትምህርትቤት ልጅዎ ለማስመዝገብ የሚፈልጉ ከሆነ ብቻ ይህንን ክፍል ሞምላት ትችላላችሁ። ወንድም ወይም እህት በሚማሩበት ትምህርትቤት ቦታ ለማግኘትና ቅድሚያ ለማግኘት የቤትዎ አድራሻ አንድ አይነት መሆን አለበት። በማህደራችን ተመዝግቦ ያለው የልጅችዎ አድራሻና አሁን በክፍል 1 ላይ የጻፉት አድራሻ አንደ አይነት መሆኑን ማረጋገጥ የርስዎ ሃላፊነት ነው።የተሳሳተ አድራሻ ከሆነ ግን ወንድም እህት በሚማሩበት ትምህርትቤት ቦታ ለመመደብ ልጅዎ ቅድሚያ ላያገኝ ይችላል።በተጨማሪም ወንድም እህተማሞቹ ለ2007 2008 የትምህርት ዘመን በዚያው ትምህርትቤት መመደብ አለባቸው።ወንድምና እህት በሚቀጥለው አመት እዛው ትምህርትቤት የማይማሩ ከሆነ ለወንድምና እህተማማች የሚሰጠውን ቅድሚያ ሊያገኑ አይችሉም።

**ክፍል 5 –** ክፍል 5ን ለሞምላት በፎርሙ በስተጀርባ ያለውን የመዋእለ ህጻናትን የምርጫ ፎርም የሚባለውን ይጠቀሙ። የትምህርት ቤቶቹ ስም በቅደም ተከተል ተዘርዝሮ ተጽፈዋል። የትራንስፖርት አገልግሎት የሚያቀርቡ ወይም የሚሰጡ ትምህርትቤቶችም በእያንዳንዱ ሰፈር ወይም ክልል መስረት ተዘርዝሮ ተጽፈዋል። አማርጭ ትምህርትቤቶችምና በከተማው ለሁሉም ስፍራዎች የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡትንም ከታች በዝርዝር ተጽፈዋል። መደበኛና ሙሉ ቀን የመዋእለ ህጻናት ፕሮግራም ያላቸው ትምህርትቤቶችም ተጽፈዋል። ግማሽ ቀን ወይም የሞንቲሶሪ ፕሮግራም የሚሰጡ ትምህርትቤቶችም ለብቻ ተጽፈዋል።

በፎርሙ ላይ የሚመርጡትን ትምህርትቤት በቅደም ተከተል ከአንድ እስከ አስር ተራ ቁጥር ድረስ ይጻፉ።የሚፈልጉትን ትምህርትቤት መምረጥ ይችላሉ ሆኖም ግን የሚመርጡት ትምህርትቤት ከክልልዎ ውጭ ከሆነ ልጅዎ የትራንስፖርት አገልግሎት ላያገኝ/ላታገኝ ይችላል/ትችላለች።

ፎርሙን ተጠቅማችሁ በክፍል አምስት ላይ ሰዎስት ትምህርትቤቶችና ፕሮግራሞች ይምረጡ። የመጀመሪያ ምርጫዎን እና የትምህርትቤቱ ተራ ቁጥር እንዲሁም የትምህርትቤቱ ስም ይጻፉ። የግማሽ ቀን ፕሮግራም ወይም የሞንትሰሪ ፕሮግራም ለማመልከት የምትፈልጉ ከሆነ አማራጭ ፕሮግራም በሚለው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ። ወደ መደበኛው ሙሉ ቀን የመዋእለ ህጻናት ፕሮግራም የምታመለክቱ ከሆነ የአማርጭ ፕሪግራም ሳጥን ባዶውን ይተዉት።ከታች ያለው ምሳሌ የሚያሳየው በመምረጫው ፎርም ክፍል አምስት እንዴት መሞላት እንዳለበት ነው። ለምሳሌ የመጀመሪያ ምርጫዎ የሙሉ ቀን ትምህርት በላውርሁስት መዋእለ ህጻናት ሲሆን ሁለተኛው ምርጫ ደግሞ በላውርሁሰት ግማሽ ቀን መዋእለህጻናት ትምህርት በሰዎስተኛ ምርጫ ደግሞ AE#2 የሙሉ ቀን ትምህርት ያሳያል።

| | School Number | | | School Name | Optional Program: Mon-tessori | Half Day | Dual Lang. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 4 | 2 | Laurelhurst | ○ | ○ | ○ |
| 2 | 2 | 4 | 2 | Laurelhurst | ○ | ● | ○ |
| 3 | 9 | 7 | 7 | AE#2 | ○ | ○ | ○ |

**ክፍል 6 (አማራጭ) –** የመጀመሪያ ምርጫዎ የሆነ ትምህርትቤት ልጅዎ ካልተመደበ እሱ ወይም እስዋ ክፍት ቦታ እስከሚገኝ ድረስ በተጠባባቂነት ሊመዘገቡ ይችላሉ። የመጀመሪያ ምርጫዎ ያልሆነ ትምህርትቤት በሌላ ትምህርትቤት ተማሪ ልጅዎ በተጠባባቂነት እንዲመዘገቡ የሚፈልጉ ከሆነም በክፍል 6 ያለውን ሳጥን ላይ ምልክት በማድረግ የሚፈልጉትን የትምህርትቤቱ ስም ይጻፉ። በክፍል 5 ላይከተዘረዘሩትን ማናቸውም ትምህርትቤቶች መምረጥ ይችላሉ። ልጅዎ ወደ የመጀመሪያ ምርጫዎ የሆነ ትምህርትቤት በተጠባባቂነት ሊመዘገብ የሚችለው በማመልከቻዎ ላይ ዝቅተኛውን ተራቁጥር ካለው ብቻ ነው። ልጅዎ በተጠባባቂነት መመዝገብ የሚቻለው በአንድ የተጠባባቂዎች ዝርዝር ላይ ብቻ ነው።

**ክፍል 7 (አማራጭ) –** አሁኑ ሰአት ልጅዎ ከምትኖሩበት ሰፈር ክልል ውጭ ትምህርቱን የሚከታተል ከሆነና አሁንም እዛው ትምህርት ቤት እንዲቀጥል የምትፈልጉ ከሆነ ብቻ እዚህ ምልክት አድርጉ። በአሁኑ ሰአት ልጅዎ የሚማርበት ትምህርት ቤት ስም እባክዎትን ይጻፉ።